# የ 1928–1933 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐርበኝነት ፤ እንዴት ፡ እንደተወጠነና ፡ እንደተስፋፋ ፡ የሚገልጥ ።

ሲ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።
(1953 ፡ ዓ.ም. ። )*

አዘጋጅ ፥ ወሴ ፡ ነጋ ።

ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፥ 2003 ፡ ዓ.ም. ።

http://www.gzamargna.net

© ወሴ ፡ ነጋ ። ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፥ 2003 ፡ ዓ.ም. ።

* የማስታወሻ ፡ ረቂቅ ፥ ያልታተመ ።



# እምቢ! ፡ አለች ፡ ኢትዮጵያ ፥ ቈንዳላ ፡ ተሠርታ ።

ቼኮስሎቫኪያ ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ነምሳ ፡ ጧት ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ፖሎኝም ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ኢጣሊያ ፡ ገበረች ፥ በጧት ፡ እጇን ፡ ሰጥታ ፤
ሁንጋሪያ ፡ ዐበረች ፥ እባርነት ፡ ገብታ ፤
ሩማንያ ፡ ዐበረች ፥ እባርነት ፡ ገብታ ፤
ቡልጋርያም ፡ ዐበረች ፥ እባርነት ፡ ገብታ ፤
ሆላንድ ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ዳንማርክ ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ኖርቬዥም ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ዩጎዝላቭ ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ግሪክም ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ሉክሳምቡር ፡ ገበረች ፥ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
ፈረንሳ ፡ ገበረች ፡ ራሷን ፡ ተላጭታ ፤
እንቢ! ፡ አለች ፡ ኢትዮጵያ ፥ ቈንዳላ ፡ ተሠርታ ።

ታረቀኝ ፡ ተፈሪ
(የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ፲ ፡ አለቃ ፤ ሰቈጤ) ፤

ኻርቱም ፥ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፥ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ፡ ም. ።

# መቅድም ።

*" የኃጥኣን ፡ ክንድ ፡ ትሰበራለችና ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ጻድቃንን ፡ ይደግፋቸዋል ። "*
*መዝ.36 ፡ (37) ፥ 17 ፤*

"ታሪክ ፡ ታሪክን ፡ ይመግባል" ፡ እንዲሉ ፥ የቀደሙ ፡ አባቶችንና ፡ እናቶችን ፡ ታሪክና ፡ ገድል ፣ ሥራና ፡ ሟያ ፣ ዝብድና ፡ ድንቅ ፡ ማስታወስ ፣ ማክበርና ፡ ማፍቀር ፥ ለዛሬውና ፡ ለመጪው ፡ ትውልድ ፡ በአርኣያነቱ ፡ እንዲበጅም ፡ ነው ።

ነጻነት ፣ እግዚእናና ፡ ዳር ፡ ድንበር ፥ የማይተኛላቸው ፡ ጠላት ፡ አለባቸውና ፥ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማያቋርጠውን ፡ መራራ ፡ ትግል ፥ ትውልዶች ፡ እየተተኩ ፡ መያያዝና ፡ ደጋግሞ ፡ ማሸነፍ ፡ የኖርባቸዋል ።

ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፥ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ስትታጠቅና ፡ ስትዘጋጅ ፡ ቈይታ ፥ በመስከረም ፡ ወር ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ ግማሽ ፡ ሚልዮን ፡ ዘመናዊ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፣ 500 ፡ የጦር ፡ ጥያራ ፣ 500 ፡ ጥሩር–ለበስ ፣ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ መድፍና ፡ ከባድ ፡ መትረየስ ፣ የመርዝ ፡ ጢስና ፡ ፈንጂ ፣ ዘመናዊ ፡ መገናኛ ፣ ሰፊ ፡ የስለላና ፡ የቈንገፋ ፡ አውታር ፡ ደርጅታ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ጦርነትን ፡ ዐውጇ ፡ ዘመተችባት ። ከስምንት ፡ ወር ፡ ውጊያም ፡ በኋላ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፥ ዝግጁነት ፡ ሳያንሰው ፥ ዐቅምና ፡ ድርጅት ፡ ጐድለውት ፥ ተፈታ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፥ ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ጉዳይ ፡ ለዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ለማቅረብ ፡ ወደ ፡ ዠኔቭ ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፥ እጃቸውን ፡ ለጠላት ፡ አልሰጡም ፤ የኢትዮጵያም ፡ መንግሥት ፡ ከነሰራዊቱ ፡ ነጻነቱን ፡ ሳያስነካ ፥ የመጣበትን ፡ ጠላት ፡ ድል ፡ ለመንሣት ፡ ያርበኝነት ፡ ተጋድሎውን ፡ ቀጠለ[1] ።

ድል ፥ በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፥ የመንፈስ ፡ እንጂ ፡ የሥጋ ፡ አለመኾኑን ፡ የነጻ ፡ ሕዝብነት ፡ ባህላቸው ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ አስተምሯቸዋልና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ ሰራዊት ፥ የጠላትን ፡ ግዙፍ ፡ ኀይል ፡ አይተው ፥ ተስፋ ፡ ቈርጠው ፦ *ተሸንፍን ፥* አላሉም! ለግፍ ፡ መልሳቸው ፡ መቼም ፡ መች ፡ አንድ ፡ ነው ፦ *እምቢ!*

*መሣሪያ* ፡ ያለው ፡ *መሣሪያውን* ፡ ይዞ ፥ የሌለውም ፡ ምርጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጅ ፥ ወንድ ፡ ሳይል ፡ ሴት ፥ ልጅ ፡ ሳይል ፡ ሽማግሌ ፥ ሳያመነታ ፣ ሳያወላውል ፥ ዥሉም ፡ ያገኘውን ፡ ይዞ ፡ ሊዋጋ ፥ ያለቀውም ፡ ዐልቆ ፥ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሙሉ ፡ ትጥቁን ፡ ታጥቆ ፥ ደረቱን ፡ ገልብጦ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ተመልሶ ፡ እመናገሻ ፡ ከተማው ፡ ሊገባ ፥ ዐርበኝነት ፡ ወጣ ።

በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ መደበኛው ፡ ጦርነት ፡ ሲያከትም ፥ ወዲያው ፥ ያርበኝነቱ ፡ ጦርነት ፥ ይፋት ፡ ውስጥ ፥ "መንግሥት" ፡ እተባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ተጭሮ ፥ ሸዋ ፡ ሮቢት ፡ ላይ ፦

*"የወንዶቹ ፡ ዥሉ ፡ አንተነኽ ፡ ጌጣቸው ፤*
*ጥቍር ፡ ጭቃ ፡ አግብተኽ ፥ ተሰማ ፡ ርገጣቸው ። "*

---

1 ባ5ቱ ፡ ዓመት ፡ ያርበኝነት ፡ ዘመን ፥ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፥ አንድም ፡ ጊዜ ፡ ቢኾን ፥ ነጻነቱን ፡ በወራሪው ፡ ፋሺስት ፡ ኢጣልያ ፡ ጦር ፡ ስላላስደፈረ ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፥ የድል ፡ በዓል ፡ እንጂ ፡ የነጻነት ፡ በዓል ፡ ሊባል ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባውምና ፤ በሚገባ ፥ የድል ፡ በዓል ፡ ሲባል ፡ ኖሯል ፤ ይኖራልም ። ኾኖም ፥ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፥ "የነጻነት" ፡ በዓል ፡ የሚለው ፡ መዘዘኛ ፡ አሰያየም ፡ ባኹኑ ፡ ሰዓት ፡ እንደገና ፡ ያንሰራራ ፡ ይመስላልና ፥ ኢትዮጵያውያን ፡ ነቅተን ፡ ልንከላከለው ፡ ይገባል ። አስቀድሞ ፡ ይኸንኑ ፡ በመጠርጠር ፡ ነው ፥ ደራሲ ፦
"... ፡ ቢነገር ፣ ቢወራ ፥ ቢተረክ ፣ ቢጻፍ ፥
ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ የፋሺስቶች ፡ ግፍ ። "
ሲል ፡ ያስጠነቀቀን ። (አዘጋጅ)

የተባለላቸው ፡ የባላምባራስ ፡ ተሰማ ፡ ርገጤ ፡ ዐርበኞች ፥ የኢጣሊያ ፡ ወታደሮችን ፡ የጫኑ ፡ 75 ፡ ካሚዮኖችን ፡ በደፈጣ ፡ አጋይተው ፡ ሲፈጁ ፥ ጫጫ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የልጅ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ማሞ ፡ ዐርበኞች ፡ እንዲሁ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ብዙ ፡ የጠላትን ፡ ሰራዊት ፡ ሲፈጁ ፥ ያርበኝነቱ ፡ እሳት ፡ ሸዋን ፡ አዳርሶ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተቀጣጠለ ።

ልክ ፡ የዛሬ ፡ 70 ፡ ዓመት ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፥ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ ካምስት ፡ ዓመት ፡ እጅግ ፡ የከፋና ፡ ዘግናኝ ፡ የፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የወረራ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፥ ኢትዮጵያ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፣ በዠግኖች ፡ ዐርበኞቿ ፡ መሥዋዕትነትና ፡ በሕዝቧ ፡ እንቢተኝነት ፥ ድል ፡ አድርጋ ፥ ነጻነቷን ፡ አረጋግጣ ፥ እግዚእናዋን ፡ አስከብራ ፥ ዳር ፡ ድንበሯን ፡ አሳፍራ ፥ እንሆ ፥ ልጆቿ ፡ ዂላችን ፡ እነጻ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በነጻነት ፡ ተወልደን ፡ ለማደግ ፡ ታድለን ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በፊት ፡ በየትኛውም ፡ ወራሪ ፡ ኀይል ፡ ያልተሸነፈችውን ፡ ኢትዮጵያ ፥ በዛሬው ፡ ዘመን ፥ ተሐድሶ ፡ ቅኝ ፡ ገዢ ፡ ኀይሎች ፡ ዳግመኛ ፡ ዘምተውባታል ። እጅግ ፡ በረቀቀ ፡ ስልት ፥ ራሳቸው ፡ አንዳች ፡ ጥይት ፡ ሳይተኵሱ ፥ በወሬ ፡ ዘመቻ ፡ ብቻ ፡ ሕዝቧን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ በማባባስና ፡ በመከፋፈል ፡ አዳክመው ፥ የሀገሪቱንም ፡ መንፈሳውያን ፣ መንግሥታውያንና ፡ ንዋያውያን ፡ ተቋሞች ፣ ሕዋሶችና ፡ ኀይሎች ፡ በእጅ-አዙር ፡ ተቈጣጥረው ፥ ርሷን ፡ ሊያገብሯት ፡ በተቃረቡበት ፡ በዘመናችን ፥ የሚያዝያ ፡ 27 ፡ ድል ፡ በዓል ፡ ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ ሙሉ ፡ ትርጒሙን ፡ ይዞ ፡ ይታሰበናል ፥ ይወቅሰናልም ።

በሚቀጥሉት ፡ ገጾች ፡ ላንባብያን ፡ የቀረበው ፡ ጽሑፍ ፥ ካርበኝነት ፡ አንጋፋ ፡ መሪዎች ፡ አንዱ ፡ የኾኑት ፡ ክቡር ፡ ሌ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ[2] ፡ (1910-2000 ፡ ዓ.ም.) ፥ በ 1953 ፡ ዓ.ም. ፡ በመከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሚኒስትር ፡ ዴታ ፡ በነበሩበት ፡ ወቅት ፥ ስላርበኝነት ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ ታሪክ ፡ ለቀረበላቸው ፡ ጥያቄ ፥ ያሰናዱት ፡ ያልታተመ ፡ የመልስ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ። ጽሑፉ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ሳይገባ ፥ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ብቻ ፡ ለማስገንዘብ ፡ የተዘጋጀ ፡ ቢኾንም ፥ በጥቂት ፡ ቃላት ፡ የሰፈረበት ፡ ታሪካዊ ፡ ምስክርነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ስለሚሰጠው ፥ ምንም ፡ ለሕዝብ ፡ ንባብ ፡ የበቃው ፡ ካ 50 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ቢኾን ፥ ዘንድሮ ፡ በምናከብረው ፡ የድል ፡ በዓል ፡ 70 ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡ ተገቢውን ፡ አጋጣሚ ፡ አግኝቷል ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።

ሌ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በ 1927-28 ፡ ዓ.ም. ፡ የጦር ፡ ትምህርታቸውን ፡ በገነት ፡ ሆሎታ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አንደኛ ፡ በመውጣት ፡ አጠናቀው ፥ በዘመናዊ ፡ ዐቅድ ፡ የተቋቋመውን ፡ ብሪጋድ ፡ በኮሎኔልነት ፡ ማዕርግና ፡ በኤታ ፡ ማዦር ፡ ሹምነት ፥ ገና ፡ ያ 17 ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ኾነው ፥ ሚያዝያ ፡ 13 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ በጣርማ ፡ በር ፡ ግንባር ፡ አዝምተዋል ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጦር ፡ ወዲያው ፡ እንደተፈታም ፥ ሚያዝያ ፡ 28 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐርበኝነት ፡ ወጡ ። ኹለት ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ እንደተዋጉ ፥ በደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ አሳሳቢነት ፥ ያርበኞችን ፡ ደብዳቤ ፡ ብሪታንያ ፡ በስደት ፡ ለሚገኙት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ እንዲያደርሱ ፡ ተጠይቀው ፥ ሳይወዱ ፡ በግዳቸው ፡ ውጊያውን ፡ ትተውና ፡ መልእክቱን ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ አመሩ ። መስከረም ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1931 ፡ ዓ.ም. ፡ የሱዳንን ፡ ጠረፍ ፡ እንደተሻገሩ ፥ በወቅቱ ፥ ሱዳንን ፡ በቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ የብሪታንያ ፡ መንግሥት ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ዐውቆ ፡ ኖሮ ፥ ጠረፉን ፡ የሚጠብቀው ፡ የብሪታንያ ፡ ጦር ፡ ይይዛቸዋል ። ጥቂት ፡ ወራት ፡ በጦር ፡ እስረኝነት ፡ ገዳሬፍና ፡ ኻርቱም ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፥ ኢጣሊያ ፡ በታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ በማወጇ ፥ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከእስር ፡ ይፈታሉ ። ኾኖም ፥ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዳይገቡ ፥ በግዞት ፡ መልክ ፡ ኻርቱም ፡ እንዲቀመጡና ፥ ከኻርቱምም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ከዋድ ፡ መድኔ ፡ እንዳያልፉ ፥ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ከሸንዲ ፡ እንዳያልፉ ፥ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ከኤድ ፡ ድዌም ፡ እንዳያልፉ ፡ በብሪታንያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይከለከላሉ ። ካንዴም ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመመለስ ፡ ሲሞክሩ ፡ እየተያዙ ፡ ተመልሰዋል ።

ኻርቱምም ፡ ኾነው ፡ ስደተኞችን ፡ ላርበኝነት ፡ በሚያደራጁበት ፡ ጊዜ ፥ ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከብሪታንያ ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ገቡና ፥ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ አስጠርተው ፥ ሶባ ፡ እተባለው ፡ የሱዳን ፡

2 የሕይወት ፡ ታሪካቸውን ፡ ዐጪር ፡ ማስታወሻ ፡ እ http://www.gzamargna.net/html/neggahailesellassie.html ፡ ይመለከቷል ። (አዘጋጅ)

ቀበሌ ፥ ዐዲስ ፡ የሚቋቋመውን ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከብሪታንያ ፡ ጦር ፡ መኰንኖች ፡ ጋራ ፡ በጣምራ ፡ እንዲመሩ ፡ አዘዟቸው ። ዐዲሱ ፡ ጦርም ፡ ተቋቁሞ ፥ መኰንኖቹና ፡ ሰራዊቱ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የመታመን ፡ መሐላቸውን ፡ በሚምሉበት ፡ ሰዓት ፥ የመሐላውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ የሚመሩት ፡ ካህን ፥ አባ ፡ ሃና ፥ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፦ *ርስዎም ፡ ይማሉ ፡ እንጂ ፥* ቢሏቸው ፤ ኮሎኔሉ ፡ ሲመልሱ ፦ *ገነት ፡ ሆሎታ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ስመረቅ ፡ የማልኩትን ፡ መሐላ ፡ አላፈረስኹምና ፥ ሌላ ፡ መሐላ ፡ አልምልም ፥ አሉ ።* አባ ፡ ሃናም ፦ *እንዴት ፡ እነሻለቃ ፡ እገሌና ፡ እገሌ ፡ ይምላሉኮ ፥* ቢሏቸው ፥ ኮሎኔሉም ፦ *እነሻለቃ ፡ እገሌና ፡ እገሌ ፡ ሲምሉ ፡ ይገባቸዋል ፥ ምክንያቱም ፡ ተሰደዋል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ያርበኞችን ፡ ደብዳቤ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አድርሶ ፡ ለመመለስ ፡ ተልኬ ፥ እንግሊዞች ፡ እሱዳን ፡ አስቀርተውኝ ፡ እንጂ ፥ ስደተኛ ፡ አይደለኹም ፤ ስለዚህ ፡ ዳግመኛ ፡ አልምልም ፥* ብለው ፡ ይኸንኑ ፡ መብታቸውን ፡ አስከብረዋል ።

ወዲያው ፥ ካዲሱ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ጐጃም ፡ ዘልቀው ፥ የኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ እንደተባረረ ፥ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ጦር ፡ በኩል ፡ ለሚኖረው ፡ ጕዳይ ፡ ኹሉ ፡ ኀላፊ ፡ ኾነው ፥ የንጉሠ ፡ ነገሥቱንም ፡ ወታደራዊ ፡ መመሪያ ፡ ይዘው ፥ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንንን ፡ እንዳልካቸውን ፡ ዐጅበው ፥ ሚያዝያ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ቀድመው ፡ ገቡ ። እንሆ ፥ ምስክርነታቸው ፤ እናንብ ።

ወሌ ፡ ነጋ ። (አዘጋጅ)

# የ 1928 – 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐርበኝነት ፤ እንዴት ፡ እንደተወጠነና ፡ እንደተስፋፋ ፡ የሚገልጥ ።

ሌ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

(1953 ፡ ዓ.ም. ። )[*]

ለዚህ ፡ ጥያቄኽ ፡ ጠቅላላ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፥ በትዝታ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መመለስና ፡ የኾነውን ፡ ማስታወስ ፡ ያሻል ።

በ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊው ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፥ ድል ፡ መመታቱ ፡ ሳይሰማ ፥ ዐቧራ ፡ ለብሶ ፥ ዐፈር ፡ መስሎ ፡ የሚመለሰው ፡ ዘማች ፡— *መሬት ፡ ከዳን ፤ ሰማይ ፡ ከዳን ፤ ሰራዊቱን ፡ ረኀብ ፡ ፈታው ፥ ሳይዋጋ ፡ ተመለሰ ፥ ጃንሆይም ፡ ያሉበት ፡ አይታወቅም ፤ የኛ ፡ ሰው ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ኾኖ ፡ እያስለቀቀለት ፥ ጠላት ፡ ጥይት ፡ ሳያጮኽ ፡ ይገሠግሣል* ፥ እያለ ፡ የሚነዛው ፡ ወሬ ፥ ለግማሹ ፡ ለሞት ፡ የሚያስቈርጥና ፡ ለመዋጋት ፡ የሚያስታጥቅ ፡ ቢኾንም ፥ ላብዛኛው ፡ ሆድን ፡ የሚያባባ ፥ ገላን ፡ የሚያርዕድ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ወሬ ፡ ሲታመስ ፣ ሲናደድ ፣ ሲናጥም ፡ የሰነበተው ፡ ያዲስ ፡ አበባና ፡ ያካባቢዋ ፡ ሕዝብ ፥ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፥ ኀሙስ ፡ ዕለት ፡ እመናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ አለብዙ ፡ ግርማ ፡ ሲገቡ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ድል ፡ መነሣት ፡ ተረዳው ። በየቤቱ ፥ ወንዱ ፡ መሞትን ፡ ቈረጠ ፤ መሣሪያና ፡ አዝማች ፡ እንዲሰጡት ፡ ሲጥይቅ ፡ ተሰብስቦ ፡ እግቢ ፡ ወጣ ። አዝማች ፡ ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተን ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ተቀበለ ፥ ግንባርም ፡ የበረኽን ፡ ጐራ ፡ ተሰጠው ።

ባለመታደል ፡ ግን ፥ ኹሉም ፡ አልኾነለትም ። ቅዳሜ ፡ ጧት ፥ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ አገር ፡ ተሻገሩ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ከተማውን ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ባወደው ፡ ጊዜ ፥ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብ ፡ የሚያደርገውን ፡ ዐጣው ። የጭንቁን ፡ ጨለማ ፡ ለጊዜው ፡ ያበሩለት ፥ ለኹሉም ፣ በኹሉም ፣ ኹሉም ፡ የኾኑት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፥ እንደ ፡ ኮከብ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ሲለዩት ፥ የተገፈፈው ፡ ጨለማ ፡ እንደገና ፡ ወደቀበት ። ሰምቶት ፣ ገምቶት ፣ አይቶት ፡ የማያውቀው ፣ የማያምነው ፡ ነገር ፡—

- ድል ፡ ተነሥታ ፡ የማታውቀው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድል ፡ መመታት ፤
- ኢትዮጵያን ፡ ለቆ ፡ የማያውቀው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጪ ፡ መሰደድ ፤
- በታሪክ ፡ ደርሶ ፡ የማያውቀው ፡ የነጭ ፡ መግዛት ፥ ጠቅላላ ፡ ባርነት ፥ ጠቅላላ ፡ ውርደት ፥ ጠቅላላ ፡ ሞትም ፤

ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ደርሰው ፡ ሲያይ ፥ ድርጊቱ ፡ እምነቱን ፡ አናጋው ፥ ከእውን ፡ መኖሩም ፡ አጠራጠረው ። ጠላትን ፡

[*] በ 1953 ፡ ዓ.ም. ፡ በመከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሚኒስትር ፡ ዴታ ፡ በነበሩበት ፡ ወቅት ፥ ስላርበኝነት ፡ ያምስት ፡ ዓመት ፡ ታሪክ ፡ ለቀረበላቸው ፡ ጥያቄ ፡ ያሰናዱት ፡ ያልታተመ ፡ የመልስ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ።

ለመመለስ ፡ የመዋጋት ፡ ፈቃዱና ፡ ተስፋ ፡ መቍረጡ ፡ ተቀላቀሉበት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ዅሉም ፡ በየደጁ ፡ የጠመንጃውን ፡ መተኰስና ፡ የጥይቱን ፡ መግደል ፡ መሞከር ፡ ዠመረ ። ጠመንጃና ፡ ጥይትም ፡ የሌለው ፥ ካለበት ፡ ሊዘርፍ ፡ ተነሣ ። ባገኘም ፡ ቍጥር ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፥ ተኰሰ ፡ ሲፈትን ፡ ድርጊቱ ፡ ተስፋፋ ፤ በከተማው ፡ ሞላ ። ያዲስ ፡ አበባም ፡ ግብ-የለሽ ፡ መጋደልና ፡ ዘረፋ ፡ በጠመንጃ ፡ ተኵስ ፣ በሴትና ፡ በሕፃን ፡ እሪታ ፡ መኻከል ፥ ሳይታወቅ ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ተፈጸመ ።

ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፥ ቃጠሎው ፡ ሲበርድ ፥ ወደ ፡ እብደት ፡ ያመራው ፡ የነዋሪው ፡ ሕዝብ ፡ ንዴት ፡ ሲያቋርጥ ፥ ኀዋው ፡ ሲቀዘቅዝ ፥ ጠላት ፡ በዐመዱ ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ ገባ ።

የጠላትን ፡ ፈለግ ፡ እየተከተለ ፥ መንግሥት ፣ ጣርማ ፡ በር ፣ ጫጫ ፡ ሲፈነዳ ፡ የመጣው ፡ ያርበኝነት ፡ እሳት ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፡ ብርሃኑን ፡ ተከለ ። ልጁም ፡ ዐዋቂውም ፣ ወንዱም ፡ ሴቱም ፦ *እንቢ! እንሞታለን ፡ በነጻነት ፡ ሕይወት ፥* ሲል ፡ ተከተለው ። ነጻነትንና ፡ ክብሯን ፡ የሚያፈቅሩ ፥ ተባታዊ ፡ መንፈስ ፡ ያላቸው ፡ ዐርበኞች ፡ ባራቱ ፡ ማእዝናት ፡ ተነሡ ፥ ያባቶችንም ፡ የዠግንነት ፡ ጋሻ ፡ አነገቡ ።

ከታላቁ ፡ ጦርነት ፡ የተመለሱት ፡ የጦር ፡ አዝማቾች ፥ እነክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ካሳ ፥ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ ዐርበኞች ፡ መሰብሰብ ፡ ዠመሩ ። የጐጃምን ፡ ጦር ፡ አዝምተው ፡ የነበሩ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ጦርነታቸውን ፡ ባለማቋረጥ ፥ የተረፉቸውን ፡ ሰራዊት ፡ ይዘው ፥ ሊከላከሉበት ፡ ወደመደቡት ፥ ወደ ፡ ጐሬ ፡ አመሩ ። ዝናቸውን ፡ የሚያውቁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶችና ፡ የገነት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጦር ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ተከተሏቸው ። በትግሬ ፥ እነደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሕይወት ፡ መሸሻና ፡ ቀኛዝማች ፡ ዐባይ ፡ ካሳ ፤ በዋግ ፥ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ኀይሉ ፡ ከበደ ፤ በላስታም ፥ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ወሰን ፡ ካሳና ፡ የኤርትራ ፡ ዐርበኞች ፥ እነቀኛዝማች ፡ ዐምዶም ፥ ጦርነቱን ፡ ባለማቋረጥ ፡ ውጊያቸውን ፡ ቀጠሉ ። እንደዚሁም ፥ በሐረርጌ ፣ ባሩሲና ፡ በባሌ ፥ የተመለሰው ፡ ዘማች ፡ ላርበኝነት ፡ ተሰለፈ ። በሲዳሞ ፡ ከዘመተው ፡ ጦር ፡ የተረፈው ፥ በክቡር ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ መሪነት ፥ ውጊያን ፡ ለመቀጠል ፡ ሲዘጋጅ ፥ በከፋም ፡ በደጃዝማች ፡ ገዛኸኝ ፡ መሪነት ፡ ዐርበኝነት ፡ ተወጠነ ።

ክረምቱ ፡ ሲያደፋጭ ፥ መንገዱ ፡ ሲዘጋ ፥ ጠላትን ፡ በየስፍራው ፡ ገጠሙት ፤ ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሲያንቀሳቅሱት ፡ ክረምቱ ፡ ጠባ ። ነገር ፡ ግን ፥ ተከታዩ ፡ የመፀው ፡ ወራት ፥ ያርበኞች ፡ መፈተኛ ፡ የኾኑ ፡ ጦርነቶች ፡ በየስፍራው ፡ ተፈጸሙና ፥ ብዙዎች ፡ የጦር ፡ አለቃዎች ፡ ተሰደዱ ፤ ብዙዎችም ፡ መኳንንት ፡ ተማርከው ፡ ከሥራ ፡ ውጭ ፡ ሲኾኑ ፥ እነደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ፣ ደጃዝማች ፡ ፍቅረ ፡ ማርያም ፡ ገብሬ ፣ ደጃዝማች ፡ ኀይሉ ፡ ከበደ ፣ እነጅማ ፡ ሰንበቴ ፣ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፣ ፊታውራሪ ፡ ኀይሌ ፡ አባ ፡ መርሳ ፣ ግራዝማች ፡ አበራ ፡ ግዛው ፡ ያሉት ፡ ዠግኖች ፡ ደግሞ ፥ ዕድላቸው ፡ ኾኖ ፥ በሞት ፡ ሲለዩ ፥ ሞያቸው ፡ የመረጣቸው ፡ ዐርበኞች ፥ እነግራዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፣ ባላምባራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፣ ልጅ ፡ ኀይል ፡ ማርያም ፡ ማሞ ፣ ሻለቃ ፡ መስፍን ፣ የገነት ፡ መኰንኖች ፣ ፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ አባ ፡ ኮራን ፣ ባላምባራስ ፡ ዘውዴ ፡ አባ ፡ ፈርዳ ፣ ልጅ ፡ ግዛቸው ፡ ኀይሌ ፣ ቀኛዝማች ፡ ተሰማ ፡ ርገጤ ፣ ባላምባራስ ፡ በሻኽና ፡ ... ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡ ዐርበኞች ፥ እንደየመጠናቸው ፥ በሸዋ ፡ ቀርተው ፡ ውጊያቸውን ፡ ቀጠሉ ።

በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ በሸዋ ፡ የተፈጸሙት ፡ ጦርነቶች ፡ የኢጣሊያን ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ቀጥተኛ ፡ ኀይል ፡ አለመጠን ፡ እያደከሙት ፡ ቢኼዱም ፥ ካርበኞችም ፡ በኩል ፡ የተሰለፉት ፡ ሰራዊቶች ፥ የውጊያ ፡ ልምድ ፡ የሚያካኺደው ፥ በሞት ፡ ለውጥ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ከቍጥራቸው ፡ የሚቀነሰው ፡ ጥቂት ፡ አልነበረም ። በዐርበኝነት ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፥ አብርሃ ፡ ደቦጭ ፡ (ሐማሴኔ)ና ፡ ሞገስ ፡ አስገዶም ፡ (ሠራዬ) ፡ የተባሉት ፡ ኹለት ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፥ በግራሲያኒና ፡ በጦር ፡ አለቃዎቹ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፥ ኢጣሊያኖች ፡ ሲበቀሉ ፥ ለውጡን ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚያናጋ ፡ የሰው ፡ መፍጀት ፡ ሥራ ፡ ባዲስ ፡ አበባና ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከተሞች ፡ ስለፈጸሙ ፥ በተቀነሰባቸው ፡ ልክ ፡ እንደገና ፡ ዐባሪዎች ፡ አገኙ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፥ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ዕድል ፡ ኾኖላቸው ፥ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ መዠመሪያ ፡ ወሮች ፡ ላይ ፥ የጐጃም ፥ ባራተኛው ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡

የበጌምድር ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ዐርበኞች ፡ ስላየሉላቸው ፥ የጦርነቱ ፡ ቀንበር ፡ ተከፈለላቸውና ፥ እንደገና ፡ በሰፊው ፡ በመሥራት ፡ የመደራጃ ፡ ፋታ ፡ አገኙ ።

የኢጣሊያኖች ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፥ ለደንበኛ ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ በሚያስፈልጉት ፡ በሰውና ፡ በመሣሪያ ፡ ኀይል ፣ በመጓጓዣና ፡ በመደማመጫ ፡ ድርጅት ፡ የተሟላ ፡ ኾኖ ፥ ባርበኞች ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ብልጫ ፡ ልክ ፡ ባይኖረውም ፥ ያርበኞች ፡ ጦር ፥ በውጊያ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፥ በቅልጥፍናና ፡ ራስን ፡ ችሎ ፡ በመንዘር ፣ በቈራጥነትና ፡ በመጋደል ፡ ፈቃድ ፡ በጣም ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ከሚደረጉት ፡ ግጥሚያዎች ፡ ውስጥ ፥ ባብዛኛዎቹ ፡ የስፍራውን ፡ ድል ፡ የሚያገኘው ፡ ርሱ ፡ ነበር ። ይኹን ፡ እንጂ ፥ ጠላት ፡ በተሸነፈ ፡ ቍጥር ፥ ዐዲስ ፡ ጦር ፡ ቀይሮ ፡ እንደገና ፡ ሲዋጋ ፥ ዐርበኞች ፥ ከመዠመሪያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፥ የሚያጋፍጡት ፡ ያንኑ ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ብሎ ፡ ብሎ ፡ መጨረሻውን ፡ መሸነፍና ፡ መመለስ ፥ ቍስለኛውን ፡ ለማሳረፍ ፡ በቀላሉ ፡ ወደማድረስ ፡ ስፍራ ፡ መገለል ፡ የሚኖርበት ፡ ርሱ ፡ ነበር ።

ዐርበኞች ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ደካማ ፡ መኾናቸው ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ሊሰጣቸው ፡ የሚገባው ፡ ድካማቸው ፡ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ኾኖ ፡ መቅረቱ ፡ ይሰማቸው ፡ ነበርና ፥ በሰውና ፡ በመሣሪያ ፣ በሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ነገር ፡ እንደፈለጋቸው ፡ ለመኾን ፡ እንዲችሉ ፥ የጦር ፡ ኅብረት ፡ አድርገው ፡ አገርንም ፡ በፖለቲካ ፡ ሥልጣን ፡ ለማስተዳደር ፡ ዘወትር ፡ ይሞክሩ ፡ ነበር ።

ዳሩ ፡ ግን ፥ የቀደመ ፡ የሕዝብ ፡ የሥልጣን ፡ አወራረስ ፡ ያልነበረና ፡ ያልተለመደ ፡ ከመኾኑ ፡ ጋራ ፥ ዐዲስም ፡ ዐይነት ፡ ሥርዐት ፡ አውጥቶ ፡ ለመሥራትም ፥ በጊዜው ፡ የነበሩት ፡ ሹማምት ፥ ለጋራ ፡ ዐይነተኛ ፡ ጥቅም ፡ ሲሉ ፥ በግል ፡ ግብዝ ፡ ጥቅማቸው ፡ መበለጥን ፡ የማይፈቅዱ ፡ ሲኾኑ ፥ ጠላትም ፡ ይህ ፡ ኅብረት ፡ እንዳይገኝ ፥ ፋታ ፡ ባለመስጠት ፡ ይወጋቸው ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ በየጊዜው ፡ ያደርጉት ፡ የነበረው ፡ ሙከራ ፡ ፍሬ ፡ ሊሰጣቸው ፡ አልቻለም ።

ከኢትዮጵያ ፡ የተማሩ ፡ ወጣቶች ፥ አብዛኛዎቹ ፡ ተከትለዋቸው ፡ የነበሩት ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ጐሬ ፡ ላይ ፡ ጊዜያዊ ፡ መንግሥት ፡ አቋቁመው ፥ የመላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ኅብረት ፡ ሊያገኙ ፡ ቃጥተው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ዕቅድ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ምን ፡ ያኽል ፡ ሊጐዳው ፡ እንደሚችል ፡ ጠላትን ፡ ስላልተሰወረው ፥ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፥ ያለውን ፡ ኀይል ፡ አፍስሶ ፡ በመውጋት ፥ ደኅኛውን ፡ ዕቅድ ፡ አጨናገፈው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፥ የሸዋ ፡ ዐርበኞች ፥ አንድ ፡ መኾን ፡ ትርፍ ፡ ያለው ፡ መኾኑን ፡ መከራው ፡ ስለ ፡ መከራቸው ፥ በጠቅላላ ፡ ምርጫ ፡ ጠቅላይ ፡ አዝማቻቸውን ፡ ሾመው ፥ አገር ፡ ግዛትን ፣ ፍርድን ፣ ጦርን ፡ የሚያስተዳድሩና ፡ የሚፈጽሙ ፡ ተከታይ ፡ ኀላፊዎች ፡ በመለየት ፡ ለመሥራት ፡ ዐስበው ፥ እንዳመጣጣቸው ፡ ተራ ፥ ግራዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋውን ፣ ባላምባራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይን ፣ ደጃዝማች ፡ አውራሪስን ፣ በየጊዜው ፡ መርጠው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ቀድሞ ፡ የተናገርኹት ፡ ራስን ፡ የመውደድ ፡ ጕዳይ ፥ ከመከራውም ፡ በላይ ፥ ካርበኞች ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ አልተነሣም ፡ ነበርና ፥ አንዳቸውም ፡ቢኾኑ ፡ በዚህ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ለመሥራት ፡ ሳይቻላቸው ፡ ስምምነቱ ፡ እየፈረሰ ፡ ቀረ ።

በጐጃምም ፡ ደጃዝማች ፡ ነጋሽ ፡ በዛብኽን ፡ ሰዎች ፡ "ራስ" ፡ ብለው ፡ ሠይመው ፥ ያገሩን ፡ ዐርበኞች ፡ ለመጠቅለል ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ከማንኛውም ፡ ሙከራ ፡ ይኽኛው ፡ ተቃዋሚ ፡ ስለበዛበት ፥ ሳይሠራ ፡ ፈረሰ ። የበጌምድርም ፡ ዐርበኝነት ፡ ዐፍላውን ፡ ባገኘበት ፡ ዘመን ፥ ልጅ ፡ ዮሐንስ ፡ ኢያሱ ፡ የበላይነትን ፡ ይዘው ፡ መሾም ፣ መሻር ፥ ማዘዝ ፣ ማዋጋትም ፡ ዠምረው ፡ ነበር ። ርሳቸውም ፥ ምንም ፡ ከኹሉ ፡ የረዘመ ፡ ጊዜ ፡ በሥልጣናቸው ፡ የሠሩ ፡ ቢኾኑም ፥ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሊዘልቅላቸው ፡ ሳይችል ፡ ቀርቷል ።

እንደገና ፥ በሸዋ ፥ ባ 1931 ፡ ዓ.ም. ፥ መልአከ ፡ ፀሓይ ፡ ኢያሱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተሠኝተው ፡ ከሸዋ ፡ ዐርበኞች ፡ ገሚሱን ፡ ሲጠቀልሉና ፡ አገሩንም ፡ ሲያሳብሩ ፥ ዕድል ፡ ሳይገጥማቸው ፡ ቀርቶ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፥ ያርበኞች ፡ ኅብረት ፡ ጕዳይ ፡ የመጨረሻ ፡ ሙከራ ፡ በርሳቸው ፡ አቋረጠ ።

ይኹን ፡ እንጂ ፥ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ሙከራዎች ፡ ምንም ፡ በየስፍራው ፡ የጸኑት ፡ በጣም ፡ ላጠረ ፡ ጊዜ ፡

ቢኾንም ፥ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ እንኳ ፡ ባይኾን ፥ ለጊዜው ፡ ያርበኞችን ፡ ኀይል ፡ በየስፍራው ፡ በመጠኑ ፡ ያዳበሩ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ራስ ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ዐያሌ ፡ የጦር ፡ አዝማቾት ፡ በበጌምድር ፣ በጐጃም ፣ በሸዋ ፣ በሌላውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ ተመቻችተው ፡ ተገኙ ። የኢትዮጵያ ፡ ዐይነተኞች ፡ ዐርበኞችም ፡ ብዛት ፥ ባፍላው ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ 300 000 ፡ ባለብረት ፡ ደርሶ ፡ ነበር ። የኀብረቱ ፡ ሥራም ፥ የበለጠ ፡ በቄየበት ፡ አውራጃ ፡ ያርበኞቹ ፡ መደርጀት ፡ የበለጠ ፡ ኾኖ ፥ የበጌምድር ፡ ዐርበኞች ፡ ከሌሎቹ ፡ አውራጃዎች ፡ ይበልጥ ፡ ለጠላት ፡ አዋኪ ፡ ሲኾኑ ፥ የሸዋው ፡ ዐርበኞች ፡ ደግሞ ፡ ፈጽመው ፡ ጠላትን ፡ የሚያርገደግዱ ፡ ኾነው ፥ የስመ ፡ ጥሩው ፡ መሪያቸው ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ዝና ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያና ፡ በውጭ ፡ አገርም ፡ ገነነ ። ኢጣሊያኖችም ፥ ከዚያ ፡ ኹሉ ፡ ኀይላቸውና ፡ ጕራቸው ፡ በላይ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፡ ስም ፡ ዕርቅ ፡ ሊደራደሯቸው ፡ ተገደዱ ። በዚህም ፥ በክቡርነታቸው ፡ መሪነት ፡ በተፈጸመው ፡ ዐዲስ ፡ ዐቅድ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ልዩ ፡ የዐርበኝነት ፡ ዘመን ፡ ተከፈተ ። በየስፍራውም ፡ የሚዳከሙት ፡ ዐርበኞች ፡ እንደገና ፡ ሞልተውና ፡ ዳብረው ፥ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የተዠመረውን ፡ የነጻነት ፡ ጦርነት ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ በየስፍራው ፡ መሳተፍ ፡ ዠመሩ ።

በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፥ የኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፡ ኀይላቸውን ፡ የሚያዋሕድ ፡ አንድ ፡ የጦርና ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ አለማብጀታቸው ፥ ወይም ፡ በቂ ፡ ግንኙነት ፡ አግኝተው ፥ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጠቅላይ ፡ እንደራሴ ፡ አለማግኘታቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ለማዋሐድና ፡ ውጤቱን ፡ የበለጠ ፡ ለማድረግ ፡ ከልክሏቸው ፡ እንደ ፡ ኖረ ፡ ኹሉ ፥ ኀይላቸውን ፡ አጣጭቶት ፡ መቄየቱ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ይኸንንም ፡ ሲያመዛዝኑት ፥ ኢጣሊያኖችን ፡ በራሳቸው ፡ ኀይል ፡ ብቻ ፡ ለማሸነፍ ፡ የሚያስችላቸውን ፡ ዕድላቸውንም ፡ ምናልባት ፡ ቀጭቶባቸውም ፡ ይኾናል ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ።

የኾነው ፡ ኾኖ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፥ ምንም ፡ በስፍራና ፡ ባሠራር ፡ አንድ ፡ ሊኾኑ ፡ ባይችሉ ፥ ለዘለዓለም ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ በአምላክ ፡ የተፈጠረች ፡ ኢትዮጵያ ፥ በፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ልትጠፋ ፡ የባሕርይ ፡ ሕግ ፡ አይፈቅድም ፡ ሲሉ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ዘለዓለማዊነት ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ጽኑ ፡ እምነት ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ መመለስ ፡ ረገድ ፡ የሚያኖሩት ፡ ተስፋ ፡ ፍጹም ፡ ኾኖ ፥ ኹሉም ፡ በስማቸው ፣ ለስማቸው ፡ ሲጋደሉ ፡ ቄዩ ። ኋላም ፥ ከንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ግንኙነታቸው ፡ እያደር ፡ እየተሻሻለ ፡ እየኼደ ፥ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፥ ለነጻነት ፡ ጦርነት ፡ ሱዳን ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ ለሚደረገው ፡ ፖለቲካዊ ፡ ፍተሻ ፡ ኹሉ ፥ አንድ ፡ ልብ ፣ አንድ ፡ ግንባር ፡ ኾነው ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ አንዳችም ፡ ስንፍ ፡ ባለመቀበል ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፣ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውንም ፡ ለመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠያቂና ፡ አስገዳጆች ፡ ኾነው ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥታቸው ፡ የተላከላቸውን ፡ የእንግሊዞችን ፡ ርዳታ ፡ ተቀበሉ ። የነጻነትንም ፡ ጦርነት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ ከበውና ፡ በትእዛዛቸው ፡ ተመርተው ፥ በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ ዐጥንታቸውን ፡ ከስክሰው ፣ ሥጋቸውን ፡ ጐዝጕዘው ፣ በድል ፡ አድራጊ ፡ ግርማና ፡ ክብር ፡ ዐጅበው ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ ኢትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ አገቧቸው ።

ዐርበኞች ፡ ይኸንን ፡ የተቀደሰና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነት ፡ ለመቸውም ፡ የዋጀ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ለትውልድ ፡ ሲያወርሱ ፥ ማንኛቸውም ፡ ታላቅ ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ አለታላቅ ፡ ድካም ፡ እንደማይገኝ ፡ ዐውቆ ፡ መተው ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ የደረሰባቸው ፡ የሥጋና ፡ የመንፈስ ፡ ፈተና ፡ ከቶ ፡ ተነግሮ ፡ አያልቅም ፥ ተወርቶም ፡ አይታመን ። በኹለት ፡ ቀንበር ፥ በጠላት ፡ ጭካኔና ፡ ባርበኞች ፡ ችግር ፡ ተይዞ ፥ ከነርሱ ፡ ይበልጥ ፡ ይሠቃይ ፣ ይደክም ፣ ይከስርም ፡ የነበረው ፡ ግን ፥ የከተማ ፡ ነዋሪውና ፡ ዐርሶ–በሌው ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባላገር ፡ ነበር ። ስለዚህም ፥ ያርበኞች ፡ ታሪክና ፡ ስም ፡ ሲነሣ ፥ ታላቁን ፡ አገልግሎት ፡ የፈጸመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሊረሳ ፡ አይገባም ፡ በማለት ፡ ልጠቅሰው ፡ እወዳለኹ ።

## ያዲስ ፡ አበባ ፡ መለቀቅ ፡ የምሥራች ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በድል ፡ አስለቅቀው ፡ በያዙት ፥ ከድል ፡ አድራጊዎች ፡ ዐርበኞቻቸውና ፡ የጦር ፡ ሰራዊታቸው ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ በተገኙበት ፥ በጐጃም ፡ ርእስ ፡ ከተማ ፥ በደብረ ፡ ማርቆስ ፥ ከምሽቱ ፡ ባንድ ፡ ስዓት ፡ ግድም ፡ እንደ ፡ ተሰማ ፥ በሰራዊቱ ፡ መኻከልና ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ታላቅ ፡ ፍሥሓ ፡ ኾነ ። ጊዜውም ፡ የፈቀደለት ፡ ሥርዐተ ፡ ወግ ፡ ስለዕለቱ ፡ ደስታ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ማታዉኑ ፡ ተፈጸመ ።

ወዲያውም ፥ የግርማዊነታቸውን ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ የመላክ ፡ ጕዳይ ፡ ስለተደቀነ ፥ ለዚህ ፡ መልእክት ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ማታዉኑ ፡ ሲመረጡ ፥ እኔም ፡ በጦሩ ፡ በኩል ፡ ለሚኖረው ፡ ጕዳይ ፡ ኀላፊ ፡ ኾኜ ፡ በክቡርነታቸው ፡ ሥር ፡ እንድሠራ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ታዘዝኹ ። መልእክቴንም ፡ እዳር ፡ ለማውጣት ፡ የሚረዱኝ ፡ ሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊና ፡ ሻለቃ ፡ ዐቢይ ፡ አበበ ፡ ተሰጥተውኝ ፥ ሚያዝያ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ ጧት ፥ ለጊዜው ፡ ለመዋጊያ ፡ በተለወጠ ፡ ባንድ ፡ የመንጓጕ ፡ "ዡንከር" ፡ አየር–ዥበብ ፡ (አይሮፕላን) ፡ ተሳፍረን ፥ ጕዟችንን ፡ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ቀጠልን ።

የጐጃምን ፡ ድንበር ፡ ለመሻገር ፡ ዐባይ ፡ አፋፍ ፡ ስንደርስ ፥ ኹለት ፡ አዳኝ ፡ የኢጣሊያ ፡ በራሪዎች ፡ ወደ ፡ አየር–ዥበባችን ፡ ሲገሠግሡ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፥ ላንዲት ፡ ደቂቃ ፡ ያኽል ፡ ፦ *ለመልእክታችን ፡ ላንደርስ ፡ ነውን ።* የሚል ፡ ሐሳብ ፡ መጥቶብን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ አሮጌው ፡ አየር–ዥበብ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ መትረየስ ፡ የተኰሰ ፡ ድምፅ ፡ ሲያሰማቸው ፥ ወደመጡበት ፡ ተመልሰው ፡ ስለጠፉ ፥ ምንም ፡ ነገር ፡ ሳይደርስብን ፥ ሚያዝያ ፡ 5 ፡ ቀን ፥ በኹለት ፡ ሰዓት ፡ ግድም ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በደኅና ፡ ደረስን ። ከእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ ጋራ ፡ ጧቱኑ ፡ ተገናኝተን ፡ ጕዳያችንን ፡ ተለዋወጥን ። እንደ ፡ ወረድንም ፥ ግር ፡ አለን ። ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ምንም ፡ አጥርተን ፡ የምናውቀው ፡ የነበረ ፡ ቢኾንም ፥ ፈጽሞ ፡ ተለዋወጠብን ። የነዋሪው ፡ የኢጣሊያ ፡ ሕዝብና ፡ የካራቢኒዬሪው ፡ ብዛት ፥ በየስፍራው ፡ ተማርኮ ፡ የታጐረው ፡ የኢጣሊያ ፡ ሰራዊት ፡ ዐይነትና ፡ ቍጥር ፡ ሲታይ ፥ አንድም ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ያጠፋ ፡ ውጊያና ፡ ግድያ ፡ የተደረገ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ።

ግርማዊነታቸውን ፡ ስንሰናበት ፡ ከተቀበልኹት ፡ ጠቅላላ ፡ መልእክት ፡ ውስጥ ፡ ዋናዎቹ ፡ ነገሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ፦

- በግርማዊነታቸውና ፡ በእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ መኻከል ፡ አገናኝ ፡ መኰንን ፡ መኾን ፤
- ዐርበኞችንና ፡ በአገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ጦር ፡ መሰብሰብና ፡ የነጻነትን ፡ ጦርነት ፡ ለመቀጠልና ፡ ያዲስ ፡ አበባንና ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጸጥታ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ማሠምራት ፤
- በኢትዮጵያና ፡ በእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ ሰራዊቶች ፡ መኻከል ፡ የተግባር ፡ መሳተፍና ፡ ሙሉ ፡ የፈቃድ ፡ አንድነት ፡ እንዲኖር ፡ ማድረግ ፤
- ያዲስ ፡ አበባን ፡ ጸጥታ ፡ በተለይ ፡ ማረጋገጥ ፤
- የኢጣሊያኖችና ፡ ግብር–ዐበሮቻቸው ፡ የኾኑት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሕይወትና ፡ ንብረት ፡ በቂም ፡ በቀል ፡ መንፈስ ፡ እንዳይነካ ፡ መጠበቅ ፤
- በጠቅላላው ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ሕዝብ ፥ በተለይ ፡ ያርበኞችን ፡ መንፈስ ፡ የሚያስቈጣ ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙትን ፡ የፋሺስት ፡ ግብር–ዐበሮች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በተለየ ፡ ማኖር ።

ይኽንን ፥ በጠቅላላው ፡ ሰፊና ፡ ከባድ ፡ የኾነ ፡ ተግባር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲጥሉብኝ ፥ ለመፈጸሚያው ፡ የሚያገለግሉኝንም ፡ ምክርና ፡ መመሪያዎች ፡ ዐብረው ፡ ሲሰጡኝ ፡ ፈቅደው ፥ ትዝ ፡ እንደሚለኝ ፥ ማንኛቸውንም ፡ ጕዳይ ፡ እንዳማክራቸው ፡ እነክቡር ፡ ሊጋባ ፡ ጣሰው ፡ ዋለሉና ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡

እግዚአብሔር ፥ ከንቲባ ፡ ገብሩ ፡ ያሉበትን ፡ የታማኞቻቸውን ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ ካስጻፉኝ ፡ በኋላ ፥ በተለይ ፡ ሲያነጋግሩኝ ፥ በተለይ ፡ ዐደራ ፡ ያሉኝና ፡ ያስማሉኝም ፥ እኔም ፡ ራሴም ፡ ብኾን ፥ ልጅነት ፡ ይዞኝ ፥ በማንኛውም ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ማንኛውንም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ ኢጣሊያዊ ፡ እንዳላጕላላና ፡ እንዳልገድል ፡ ነበር ።

ዐዲስ ፡ አበባም ፡ እንደ ፡ ገባን ፥ ይኸንን ፡ ንጉሣዊ ፡ ዐደራና ፡ ምክር ፥ በቃሉና ፡ በመንፈሱ ፡ ሙሉ ፡ አክብረን ፥ ጓደኞቼና ፡ እኔ ፡ ሰፈራችንን ፡ እታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፥ ዕንጨት ፡ ቤት ፡ በማድረግ ፡ ሥራችንን ፡ ቀጠልን ።

ያዲስ ፡ አበባን ፡ ከተማ ፡ በኹለት ፡ ከፍለን ፥ ከገፈርሳ ፡ የካ ፡ ከሚዘልቀው ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የሚያየውን ፡ ግንባር ፥ ሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ ፤ ወደ ፡ ደቡብ ፡ የሚያየውን ፡ ደግሞ ፡ ሻለቃ ፡ ዐቢይ ፡ አበበ ፡ ተረክበው ፥ ጸጥታውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ካደረግን ፡ በኋላ ፥ ዐይነተኛ ፡ ሥራችንን ፡ ዠመርን ። የመልእክቱ ፡ ሹም ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ የሥራ ፡ መዠመሪያ ፡ ያደረጉት ፥ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በጠላት ፡ ቀንበር ፡ ለተሠቃየው ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብና ፥ ለነጻነታቸው ፡ ሲጋደሉ ፡ ለቈዩት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ዐርበኞች ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መድረስና ፥ በጥቂት ፡ ሳምንቶችም ፡ ውስጥ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገቡ ፡ መኾናቸውን ፡ ማብሠር ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ያዲስ ፡ አበባን ፡ መኳንንትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ በጠቅላይ ፡ ሹም ፡ በጸሓፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ታሪኩ ፡ አማካይነት ፡ ሰብስበን ፡ የምሥራቹን ፡ ከነገርናቸው ፡ በኋላ ፥ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፥ በየማእዘኑ ፡ የሰፈሩትን ፡ ዐርበኞች ፡ ለመጐብኘት ፡ ተነሣን ።

በመዠመሪያ ፡ ያመራነው ፥ በሞያቸውና ፡ በዠግንነታቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፡ ኹሉ ፡ የመዠመሪያውን ፡ ደረጃ ፡ ክብር ፡ ወዳገኙት ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ መሪ ፥ ወደ ፡ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ነበር ። ሰንዳፋ ፡ ከተማ ፡ ስንደርስ ፥ የከተማውን ፡ ኬላ ፡ የሚጠብቁት ፥ የክቡርነታቸው ፡ ዐርበኞች ፡ እጅ ፡ ነሥተው ፥ በትሕትና ፡ ከተቀበሉን ፡ በኋላ ፥ መድረሳችንን ፡ የሚነግር ፡ በራሪ ፡ ወደ ፡ ክቡርነታቸው ፡ በፍጥነት ፡ ላኩ ። ጕዟችንንም ፡ ስንቀጥል ፥ ከከተማው ፡ በስተሰሜን ፡ የሬዚደንሳው ፡ ግቢ ፡ በነበረው ፡ ውስጥ ፥ ክቡርነታቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እግቢው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኘው ፥ የኢጣሊያን ፡ ባንዲራ ፡ ያውለበልብ ፡ በነበረው ፡ ደቀል ፡ ላይ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ዠግንነታቸውን ፡ የመራውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አውጥተው ፥ ዐርበኞቻቸውን ፡ በ"በ" ፡ መልክ ፡ በሰፌው ፡ አሰልፈው ፥ እያደር ፡ እየቀረብን ፡ የሰልፉን ፡ ጅምላ ፡ ስንመለከተው — የጊዜው ፡ ስሜታችን ፡ አጋኖብንም ፡ እንደኾነ ፡ አላውቅ — በእውኑ ፡ ክቡርነታቸው ፡ ባንበሳ ፡ ሰልፈኛ ፡ የተከበበ ፡ ጐፈር ፡ አንበሳ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ለእጅ ፡ ሰላምታ ፡ እንደተቃረብንም ፥ ከኹለቱም ፡ በኩል ፡ ፍጹም ፡ የኾነ ፡ ትሕትናና ፡ ፍቅር ፡ በመሳውና ፥ ግርማም ፡ ባልተለየው ፡ እጅ ፡ አነሣሥ ፡ ተቃርበው ፡ ከተሳሳሙ ፡ በኋላ ፥ ኹላችንም ፡ በዚሁ ፡ መንገድ ፡ ከክቡርነታቸው ፡ ጋራ ፡ ተገናኘን ።

ወዲያውም ፥ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተላኩትን ፡ ቃል ፡ ለክቡር ፡ የጦሩ ፡ መሪና ፡ ለሰራዊቱ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ካሰሙ ፡ በኋላ ፥ ክቡር ፡ ራስ ፡ አበበም ፡ ካርበኝነት ፡ ስሜት ፡ የፈለቀና ፡ የመንፈሱን ፡ ጠል ፡ የያዘ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ተባታዊ ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ። ከንግግራቸውም ፡ እስካኹን ፡ ትዝ ፡ የሚለኝና ፡ በልቦናዬና ፡ በዐይኔ ፡ ላይ ፡ የቀረው ፡—

> *"ለነጻነት ፡ ስንጋደል ፡ የቈየን ፡ ዐርበኞች ፥ አኹንም ፡ ያለነው ፡ ለነጻነት ፡ ለመሞት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ጠላት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተባሮ ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፥ ደከመን ፡ የምንል ፡ አይደለንምና ፥ ጃንሆይ ፡ ይዘዙን ፥ እንደገና ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ያሠምሩን ፤ ጣመናችን ፡ ይርገፍ ፡ አንልም ። ዛሬ ፡ የምኞታችን ፡ ወሰን ፡ የኾነውን ፡ የግርማዊነታቸውን ፡ መመለስ ፡ ከሰማን ፥ ከቶ ፡ ሌላ ፡ አንፈልግም ፤ ስእለታችን ፡ የነበረውን ፡ ሞትን ፡ ነው ፡ እንጂ"* ፥

ሲሉ ፡ በቈረጠ ፡ የወንድ ፡ ቃል ፡ የሰጡት ፡ ማረጋገጫና ፡ ያነጋገራቸው ፡ ተባታዊ ፡ ኹኔታ ፡ ነው ።

## የሚያዝያ ፡ 27 ፡ ድል ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ።

በየደረስንበት ፥ ከዚሁ ፡ በሚቀራረብ ፡ ኹኔታ ፥ እነአቶ ፡ ይልማ ፡ በሼንና ፡ እነልጅ ፡ ፀሓዩ ፡ ዕንቈ ፡ ሥላሴን ፥ እነልጅ ፡ ከበደ ፡ ብዙነሽን ፥ እነልጅ ፡ ጃገማ ፡ ኬሎን ፥ እነልጅ ፡ ዘውዴ ፡ ጥላኹንን ፥ እነሻቃ ፡ በቀለ ፡ ወያን ፥ እነባላምባራስ ፡ ገረሱ ፡ ዱኪን ፡ በተራ ፡ አዳረስን ።

ያርበኞችንም ፡ ጒብኝት ፡ እንደ ፡ ጨረስን ፥ ከሰላም ፡ ተገዢነት ፡ ተነሥተው ፡ ተዋጊ ፡ የኾኑትን ፥ ከኢጣሊያም ፡ ባንዳነት ፡ ከድተው ፡ ካርበኞች ፡ ጋራ ፡ ያበሩትንና ፥ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ብረት ፡ ያገኙ ፡ ኹሉ ፡ ፈቀድን ። ያርበኞችና ፡ የብረት ፡ ያገኙ ፡ ጠቅላላ ፡ የመንፈስ ፡ ኹኔታና ፡ ብዛት ፡ ጦርነቱን ፡ ለመቀጠል ፡ በሰፊው ፡ የሚበቃን ፡ መኾኑን ፡ ከተመለከትንም ፡ በኋላ ፥ ከእንግሊዞች ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ ጠላትን ፡ እንዲያባርሩና ፡ ያገሩን ፡ ጸጥታ ፡ እንዲጠብቁ ፥ በሸዋ ፣ በወሎ ፣ በትግሬና ፡ በበጌምድር ፣ በወለጋና ፡ በከፋ ፣ በከንባታና ፡ በሲዳሞም ፡ በኩል ፡ የሚላኩትን ፡ ፈጥነን ፡ አስሠማራን ። ላዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፡ ጥበቃ ፡ የሚኾኑትንም ፡ ከፍለን ፡ በየምሽጉ ፡ አሰፈርን ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያና ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብ ፥ በተለይም ፡ ያርበኞች ፡ የተደሰተና ፡ መሥዋዕት ፡ ለመኾን ፡ የተዘጋጀ ፡ መንፈስ ፥ መልእክታችንን ፡ በቀላሉ ፡ ለመፈጸም ፡ ረዳን ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ሲገቡ ፥ ጥበቃቸውን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ጦር ፡ በኮሎኔል ፡ ክፍሌ ፡ ዕርገቱ ፡ ኀላፊነትና ፡ በጥንት ፡ የክብር ፡ ዘበኞች ፡ ሹማምት ፡ አቋምነት ፡ አቋቋምን ። ለጊዜው ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ጦራዊ ፡ ጸጥታ ፡ የሚያረጋግጡና ፡ ለወደፊቱም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ የሚሠሩ ፡ ያርበኞችና ፡ የስደተኞች ፡ ጦር ፡ በጥንት ፡ በገነት ፡ መኰንኖች ፡ ኀላፊነት ፡ አደራጀን ። ላዲስ ፡ አበባም ፡ ጊዜያዊ ፡ የፖሊስ ፡ ተግባርና ፡ ለወደፊቱም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዘበኛ ፡ ሰራዊት ፡ ውጥን ፡ የሚኾን ፡ የፖሊስ ፡ ኀይል ፡ በእንግሊዝ ፡ ጦር ፡ አሠልጣኝነት ፡ እንዲቋቋም ፥ ከገነት ፡ መኰንኖች ፡ ከፍለንና ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ወጣቶች ፡ መኻከል ፡ ፈቃደኞችን ፡ መርጠን ፡ ሰጠን ። የኢጣሊያኖችን ፡ ንብረት ፡ የሚጠብቅ ፡ የዘበኛ ፡ ኀይል ፡ በጥንት ፡ ያራዳ ፡ ዘበኞች ፡ ሹማምትነት ፥ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከንቲባ ፡ ሥር ፡ ተቋቋመ ። የኢጣሊያኖች ፡ ግብር-ዐበር ፡ የኾኑትንም ፡ ሰዎች ፥ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ወጣቶች ፡ የበቀል ፡ ዐይን ፡ ፊት ፡ ለማስገለልና ፡ ከዛቻቸውም ፡ ለማዳን ፡ አስቸጋሪ ፡ አልኾነብንም ።

በክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፡ ደኀኛ ፡ መሪነት ፥ ከእንግሊዞች ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፥ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ የዝግጅት ፡ ሥራችንን ፡ ከፈጸምን ፡ በኋላ ፥ የግርማዊነታቸውን ፡ የድል ፡ አድራጊነት ፡ አገባብ ፥ የጸጥታና ፡ የሰልፍ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐትንም ፡ ጒዳይ ፡ አጠናቀን ፥ ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. — ልክ ፡ የዛሬ ፡ ኻያ ፡ ዓመት — ባ 4 ሰዓት ፥ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከእንጦጦ ፡ ተነሥተው ፥ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተሰልፎ ፡ በዕልልታና ፡ በሆታ ፣ በመዝሙርና ፡ በንሴብሖ ፡ ናፍቆቱንና ፡ አድንቆቱን ፡ በሚገልጽላቸው ፡ ሕዝብ ፡ መኻከል ፡ እነጻነት ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ ዘልቀው ፥ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ በመንገዱ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ተሰልፈው ፥ ካቶ ፡ በትረ ፡ ጽድቅ ፡ ካሳ ፡ የተደረሰውንና ፡ ኮሎኔል ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ ተክሉ ፡ ያስጠኑትን ፡

*"ቅዱስ ፡ አልፋ ፡ ዖሜጋ ፡ ነኽ ፥ መቼም ፡ የማትጠፋ ፤*
*ዛሬ ፡ ለኛ ፡ ኾንከን ፡ ደገፋ ። "*

የሚለውን ፡ ቅኔ ፡ ባማረ ፡ ዜማ ፡ በሚዘምሩ ፡ ወጣቶች ፡ መኻከል ፡ ዐልፈው ፥ እመናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ዘልቀው ፥ እንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ገቡ ። የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እንደገና ፡ እጥንት ፡ ስፍራዋ ፡ አኑረው ፥ መንግሥታቸውን ፡ መልሰው ፡ የሚያቋቁሙበትንና ፡ ዐዲስ ፡ ዘመን ፡ የሚከፍቱበትን ፡ የታወቀውን ፡ ታላቅ ፡ ንግግራቸውን ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለዓለም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ አስሰሙ ።

በዚህም ፡ ንጉሣዊ ፡ ከብካብ ፡ መልእክታችን ፡ ፍጻሜውን ፡ አገኘ ፨